የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ቀን፡- ተሕሣስ 26 2015

ቁጥር፡- አ11 62/11/837

**ለኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ/ኢብአፓ/**

**አዲስ አበባ፣**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ/ኢብአፓ/ በቁጥር ኢብአፓ 461/671/2013 ጳጉሜ 3/2013 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ ፓርቲው ነሐሴ 27 ቀን 2013 ዓ.ም ያካሄደውን ጠቅላላ ጉባኤ በሚመለከት ሪፖርት አቅርቧል፡፡

ቦርዱ ታህሳስ 19 ቀን 2015 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ ፓርቲው ከሪፖርቱ ጋር አያይዞ ያቀረባቸውን ሰነዶች ከሕጉ፣ ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ እና የቦርዱ ታዛቢዎች ካቀረቡት ሪፖርት አንፃር መርምሮ ፓርቲው ነሐሴ 27 ቀን 2013 ዓ.ም. ያሻሻለው የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ላይ ያሉ ከአዋጅ ቁጥር 1162/2011 ጋር የሚቃረኑ አንቀፆች ተፈፃሚ እንዳይሆኑ እንዲሁም ጠቅላላ ጉባኤው በቀጣይ ስብሰባው አስፈላጊውን ማስተካከያ እንዲያደርግባቸው ወስኗል፡፡ በዚሁ መሠረት፡-

ሀ/በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ /ሀ/6 «የፓርቲው ፕሬዝዳንት የፓርቲው አባሎች በሚፈጽሙት ጥፋት ፓርቲውን የሚጎዱት ሆኖ ካገኘው ከፓርቲው መሰረዝና ማባረር ይችላል፡፡» የሚለው በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ አመራሮችን በተመለከተ እንዲሁም አባላትን በተመለከተ በጠቅላላ ጉባኤ እና በዲሲፕሊን ኮሚቴ ሳይወሰን ፕሬዝዳንቱ ብቻቸውን ማባረራቸው አግባብነት የሌለው በመሆኑ ይህ የደንቡ አንቀጽ ተፈፃሚ እንዳይሆን በቀጣዩ ጠቅላላ ጉባኤም አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጎበት እንዲቀርብ፤

ለ/በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 4.4 «ውሳኔዎች የሚወሰኑት ጉባኤው 50+1 ድምፅ እኩል ሲሆን የፕሬዝዳንት ድምጽ እንደ ሁለት ይቆጠራል፡፡» የሚለው የአዋጁን ማንኛውም አባል እኩል ድምጽ ያለው መሆኑን የሚገልጽ ድንጋጌ መኖር አለበት የሚለውን የሚፃረር በመሆኑ ይህ የደንቡ አንቀጽ ተፈፃሚ እንዳይሆን በቀጣዩ ጠቅላላ ጉባኤም አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጎበት እንዲቀርብ፤



ለድምጽዎ የሚያምኑን

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe

ትዊተር
@NEBEthiopia

ኢሜይል
contact@nebe.org.et

ድረ-ገጽ
www.nebe.org.et

ሐ/በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 4.6 የማእከላዊ ኮሚቴ የማእከላዊ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባላትን ከውስጡ በይፋ/በግልጽ/ ይመርጣል የሚለው በአዋጁ አንቀጽ 74/3 በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች ምርጫ በሚስጥር መሆን አለበት በሚለው መሠረት ተስተካክሎ መቅረብ ያለበት በመሆኑ ይህ የመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ ተፈፃሚ እንዳይሆን በቀጣዩ ጠቅላላ ጉባኤም አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጎበት እንዲቀርብ፤

መ/በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6.11 «. . . የግንባር ሂደት በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይጸድቃል፡፡» የሚለው በአዋጁ አንቀጽ 93 2/ሀ/ መሠረት ግንባር መፍጠር በጠቅላላ ጉባኤ ሲወሰን በመሆኑ በዚሁ አግባብ ተስተካክሎ መቅረብ ያለበት በመሆኑ ይህ የመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ ተፈፃሚ እንዳይሆን በቀጣዩ ጠቅላላ ጉባኤም አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጎበት እንዲቀርብ፤

ሠ/በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 13.3 የዲሲፕሊን ክስና ውሳኔ በተመለከተ «አባላቱን ለመከፋፈል የፓርቲው አንድነትና ጥንካሬ መሸርሸርና ፓርቲውን የሚያናጋ ድርጊት ያለመፈጸም፡፡» በምን አግባብ ሊያስከስስ እንደሚችል ግልጽ አለመሆኑ፣

ረ/በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 13.4 የዲሲፕሊን ክስና ውሳኔ በተመለከተ «. . .የግለሰቦችን ሁለንተናዊ አብአዊ የሚነካ አሉባልታ ማራመድ፡፡» በሚለው ሃሳብ አብአዊ ግልጽ አለመሆኑ፣

**በተጨማሪም፡-**

ሰ/በአዋጁ አንቀጽ 74/1/ኘ/ መሠረት የፖለቲካ ፓርቲው የውስጥ አለመግባባቶች አፈታት ሥርዓት በመተዳደሪያ ደንቡ ያልተካተተ መሆኑ፤

ሸ/በአዋጁ አንቀጽ 74/3/ መሠረት የፓርቲው አመራሮች እና በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች አመራረጥ ግልፅ፣ ነፃና ፍትሃዊ እንዲሁም በሚስጥር በሚሰጥ ድምጽ መንገድ የሚመረጡ መሆናቸውን በመተዳደሪያ ደንቡ ያልተካተተ መሆኑ ተገልፆለት አሟልቶ አልቀረበም፤

ቀ/በአዋጁ አንቀጽ 74 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ መሠረት ማንኛውም አባል እኩል ድምፅ ያለው መሆኑን የሚገልጽ ድንጋጌ በመተዳደሪያ ደንቡ አልተካተተም፣

በመሆኑም ቦርዱ ፓርቲው በቀጣይ በሚያካሂደው ጠቅላላ ጉባኤ ከላይ በተገለፀው መሠረት በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ማሻሻያዎችን አድርጎ ሪፖርት እንዲያቀርብ እያሳወቀ ቦርዱ ፓርቲው ነሐሴ 27 ቀን 2013 ዓ.ም ያካሄደውን ጠቅላላ ጉባኤ እና ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች የመዘገበ መሆኑን እንገልፃለን።

ከአክብሮት ሠላምታ ጋር

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዘርፍ

ውብሸት አየለ ጌጤ
Woubshet Ayele Gete
ኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ም/ሰብሳቢ
Deputy Chairperson National Electoral Board